የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia

## ጋዜጣዊ መግለጫ

# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ2018/19 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ አመት እቅድ አፈጻጸምን አስመልክቶ የተዘጋጀ አጭር መግለጫ

1. **መግቢያ**

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሀገራችን የባንክ ኢንዱስትሪ ውስጥ የመሪነት ሚናውን እንዳስጠበቀ ላለፉት 75 አመታት መጓዝ የቻለ ባንክ ነው፡፡ የሀገሪቱን የልማት ፕሮጀክቶችና አጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴ በፋይናንስ በመደገፍ፣ የባንክ አገልግሎት በመላ ሀገሪቱ በማስፋፋትና አዳዲስ በቴክኖሎጂ የተደገፉ የባንክ አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ የሀገሪቱን ፈጣን ልማት ተከትሎ በመንግስትና በግሉ ኢንቨስትመንት የሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ በመምጣቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም ይህንኑ የሚመጥን ምላሽ በመስጠት ላይ ነው፡፡ በተለይ እ.ኤ.አ በ2025 ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የንግድ ባንክ ለመሆን ያስቀመጠውን ራዕይ ደረጃ በደረጃ በማሳካት ላይ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ2018/19 በጀት አመት የመጀመሪያ ሩብ አመት የስራ አፈጻጸም ግምገማ እ.ኤ.አ ከጥቅምት 23-24/2011 ዓ.ም በድሬዳዋ ከተማ አካሂዷል፡፡ የባንኩ የሩብ አመት እቅድ አፈጻጸም ከሞላ ጎደል ጥሩ የሚባል ነበር፡፡

2. **የተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብ**

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ2018/19 የመጀመሪያ ሩብ አመት አጠቃላይ ተቀማጭ ሂሳብ እ.ኤ.አ ጁን 30 ቀን 2018 ከነበረበት 451 ቢሊዮን ብር 457 ቢሊዮን ብር ማድረስ ችሏል፡፡ በግለሰብ ተቀማጭ (Private Deposit) እቅዱን መቶ በመቶ ማሳካት ችሏል፡፡ ይህን እውን ለማድረግም የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል ለማበረታታትና ለማሳደግ የሚረዱ የተለያዩ እቅዶች በማውጣት ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

3. **የውጭ ምንዛሬ ግኝት**

የሀገሪቱን የልማት ጥያቄ በአግባባ ለመመለስ እንዲቻል እንደተቀማጭ ገንዘብ ማሰባሰብ ሁሉ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ባንኩ በሩብ በጀት አመቱ ከሀዋላ፣ ከውጭ ምንዛሬ እንዲሁም ከወጪ ንግድ ከ1 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ማሰባሰብ ችሏል፡፡

4. **የብድር ስርጭትና አሰባሰብ ክንውን**

በዚሁ ሩብ አመት ለልዩ ልዩ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚውል 14.4 ቢሊዮን ብር አዲስ ብድር ለደንበኞች ቀርቧል፡፡ በተጨማሪም በሩብ አመቱ 13.6 ከብድር ተመላሽ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

## 5. ጠቅላላ ሀብት እና ትርፍ አፈጻጸም

በሩብ አመቱ የባንኩ ጠቅላላ ሀብት ብር 578 ቢሊዮን ማድረስ የተቻለ ሲሆን፣ የሩብ አመት ትርፉም ከታክስ በፊት ብር 4.7 ቢሊዮን ሆኗል፡፡

## 6. የባንክ አገልግሎት ተደራሽነት እና የኤሌክትሮኒክ ባንኪንግ አፈጻጸም

የባንክ አገልግሎትን ተደራሽ ከማድረግ አንፃር የባንክ ቅርንጫፎች በአሁኑ ጊዜ ከ1,290 በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡ ሀገራዊ ቁጠባን ለማበረታታት የሚያስችል ስትራቴጂ ተነድፎ ለተግባራዊነት በሚደረገው እንቅስቃሴ የአስቀማጭ ደንበኞች ቁጥር 19 ሚሊዮን ደርሷል፡፡ ከተደራሽነት ጎን ለጎንም የአገልግሎት ጥራትን በየጊዜው በማሻሻል ተመራጭ ባንክ ለመሆን የሚደረጉ ጥረቶች ውጤታማ እየሆኑ መጥቷል፡፡

ዓለም የደረሰበትን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ወደሃገር ውስጥ በማስገባትም ህብረተሰባችንን ተጠቃሚ እያደረግን እንገኛለን፡፡ በአሁኑ ጊዜ ባንካችን ከ3.6 ሚሊዮን በላይ የካርድ ተጠቃሚዎች ያሉት ሲሆን፣ በመላ ሀገሪቱም ከ2000 በላይ ኤቲኤሞችን ከ11 ሺህ በላይ ፖስ መክፈያዎችን በልዩ ልዩ ቦታዎች በማስቀመጥ የክፍያ ሥርዓቱን ለማዘመን የሚደረገውን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ እያገዘ ይገኛል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከ1.7 ሚሊዮን በላይ የሞባይል የባንክ አገልግሎት፣ ከ39 ሺህ በላይ የኢንተርኔት የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚዎችም በመመዝገብ የአገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሲቢኢ ብር(CBE BIRR) በተሰኘው የወኪል የባንክ አገልግሎት ደንበኞች ወደ ቅርንጫፍ መሄድ ሳይጠበቅባቸው አገልግሎቶችን በቀላሉና በፍጥነት ማግኘት የሚችሉባቸውን ከ3200 በላይ ህጋዊ ወኪሎችን አፍርቷል፣ በዚህም ከ 500 ሺህ በላይ ደንበኞችን ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል፡፡

## 7. ማጠቃለያ

ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የባንኩን የ2025 ራዕይ ከማሳካት አንጻር እንዲሁም የሀገራችንን የፋይናንስ ዘርፍ ለማሳደግና የክፍያ ሥርአቱን ለማዘመን የሚረዱ የተለያዩ እቅድና ፕሮጀክቶችን በመንደፍ በሩብ አመቱ ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን የተገኘውም ውጤት አበረታች ነበር ማለት ይቻላል፡፡